ስሪት1.0 (februar 2021)

## ከማስተዋወቂያው መርሐ ግብር(ፖሮግራም) ከመካፈል ስለ መቅረት፣ፈቃድን ስል መጠየቅንና ስለ የእረፈት ወቅት ሕጎች

ከማስተዋወቂያው መርሐ ግብር መቅረትን በሚመለከት ሕጉ ከስራ መስክ ላይ ለሚካፈሉ ሰራተኞች ወይም ለስራ ሕይወት ውስጥ ከወጣው ሕግ ጋር በብዛት ተመሳሳይነት አለው። ሖኖም ግን ከዚሕ ተመሳሳይ ሕግ አንድ ለውጥ ይገኝበታል ። ይኸውም የመተዋወቂያው መርሐ ግብር ተካፋዮች ለተወሰነ ፐርስንት የሕመም ፈቃድን መውሰድን አይችሉም።

የረፍትን ወቅት በሚመለከት ግን የመተዋወቂያውን መርሐ ግብር ተካፋዮች የራሱ የሆነ ለስራ ሕይወት ከወጣው ሕግ የተለየ የሆነ መመሪያ ሕግጋቶች ወጥቶለታል።

የሙሉ ቀን ስራ የማግኘት እድል ያጋጠመዎት ከሆነ ከማስተዋወቂያው መርሐ ግብርን ከመካፈል ፈቃድ ማግኘት ይችላሉ ።

ከታመሙና በሕመሙም ምክነያት ለመካፈል ብቁ ካልሆኑ ለአውራጃው (ኮሚውኑ)፣ ለአስተማሩዎ ወይም ለልምምድ ለወጡበት ቦታ በተቻለ ፍጥነት በሕመም ምክነያተ ለመምጣት አለመቻሎትን ማስታወቅ ያስፈልጎታል።

ከመካፈል የቀሩበት ምክነያት በቂ ከሆነና ማስረጃም ማቅረብ የሚችሉ ከሆነ ግን ማስተዋወቂያ መርሐ ግብሩን ተሳታፊ በመሆንዎ የሚከፈሎኦትን አስተዋተጽዋ የማግኘት መብት ይኖሮታል። ነገር ግን በራስ ፈቃድ የመቅረት መብትዎን(egenmelding) መጠቀም ካልቻሉና የቀሩበትን ምክነያት ሐኪም በሚሰጠው የጤና መረጃ ለቀሩበት ምክነያት ማስረጅ ማቅረብ ካልቻሉ ወይም ደግሞ ለመቅረት ሕጋዊ ፈቃድ አግኝተው ካልሆነ ከሚሰጥዎት የተሳታፊ አስተዋጽዋ ላይ ለቀሩባቻው ሰአታት ወይም ቀናት ተቆራጭ ይሆናል ። ምክነያቱም በዚህ መንገዱ ከተካፋይነት መቅረት እንደ አለ በቂ ምክነያት ወይንም ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ እንደመቅረት ተደርጎ ስለሚቆጠር ነው። ያለ በቂ ምክነያት ከተካፋይነት መቅረት የማስተዋወቂያውን መርሐ ግብር የመካፈል መብትዋንና የተካፋይነት ድጎማወን ማጣትን ሊያስከትል ይችላል።

## ሕመም

በራስ ፈቃድ በሚወሰድን የመቅረት ፈቃድ ምክነያት ወይም ደግሞ በዶክተር ፈቃድና መረጃ ከማስተዋወቂያው መርሐ ግብር በሕመም ወይንመ በደረሰቦት አደጋ ምክነያት ለመካፈል ከታገዱ መቅረት ይቻላል። በራስ ፈቃድ በሚወሰን የመቅረት መብትዎን ለመጠቀም በጽሁፍ ወይንም በቃል ለአውራጃው ወይም ለኮሚውኑ፣ ለማስተዋወቂያው መአከል፣ ለመርሐግበሩ አማካሪዎ ለሁኑት ወይም ለአስተማሪዋ መታመሞትን ማስታወቅ ይኖርቦታል።

• ነገር ግን የማስተዋወቂያውን መርሐ ግብር ለ 8 ሳምንታት ያሕል ከተካፈሉ በሁላ ብቻ ነው በራስ ፈቃድ በሚወስን የመቅረት መብትን በመጠቀምና ከመርሐ ግብሩ ተካፋኝነት የመቅረት መብት የሚኖርዎት። ስለዚህ በመጀመሪያዎቹ 8 ሳምንታት ወቅት በሕመም ምክነያት በመርሐ ግበሩ መሳተፍ ካልቻሉ ከአኪም የጤና መረጃ መቅረብ ይኖርቦታል።

• በራስ ፈቃድ በሚወሰን የመቅረት መብትን 4 ጊዜ በ12 ወራት ውስጥ የመጠቀም እድሎ አሎት ።በራስ ፈቃድ በሚወስን የመቅረት መብት በአንድ ጊዜ ሊወሰድ የሚቻለው እስከ 3 ቀን ብቻ ነው ።

• ከሶስት ቀናት በላይ የታመሙ ከሆነ ደግሞ የሀቂም የጤና ማረጋገጫ ማቅረብ ያስፈልጋል ። በአንድ አመት ውስጥ 4 ግዜ እስከ በተከታታይ 3 ቃናት ብቻ ነው በራስ ፈቃድ የመቅረት መብትዎን ለመጠቀም የሚችሉት። እንዚህን መብቶችን ተጠቅመው ከጨረሱ በሆላ ግን የሃኪም የጤና መረጃ ማቅረብ ይኖርቦታል ።ይኸውም በቂነት ባለው ምክነያት የመቅረት መብትዎ እንዲከበር ለማድረግ ያበቃል።

አንደ ወይም ሁለት ልጆች ከአሎት ልጅ ሲታመም በ12 ወራት ውስጥ የ10 ቀናት እቤት ቀርቶ ልጅ የማስታመም መብት ይኖሮታል።

ከሁለት ልጆች በላይ ከአልዎት ግን በልጅ መታመም ምክነያት እስከ 15 ቀናት ከመርሐ ግብሩ ተካፋይነት ነጻ መሆን ይችላሉ።

ሌጣ ልጅ አሳዳጊ ከሆኑና (ለብቻዎ ልጅ አሳዳጊ ከሆኑና) አንድ ወይም ሁለት ሎጆች ከአሎት 20 ቀናት ማስታመሚያ ሲኖርዎት ከዛ በላይ ልጆች ከአሎት ግን 40 ቀናት ይኖሮታል።

ልጆች የሚጠብቅልዎት ግለሰብም (ማግዚት)ቢታመም እንደዚሁ ከላይ የተጠቀሱት መብቶች ይኖሮታል። ከተካፋየነት የሚቀሩበት ምክነያት ግን 3 ቀናት በላይ ከሆነ አውራጃው ታመመ ለተባለው ልጅ ወይም ጠባቂ/ማግዚት ለመታመሙ የሀኪም የጤና ማረጋገጫ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ሊጠይቅ ይችላል።

### ከማስተዋወቂያው እቅዱ ፈቃድ ጊዜ ስለማግኘት

*ከእርግዝና ጋር በተያያዘ የእረትፈት ጊዜ*

ነፍሰ ጡር ከሆኑ ከማስተዋወቂያ እቅዱ ተካፋይነት ለእርግዝና ጋር የተያያዘ የጤና ቅጥጥር ለማኘት በሚያስፈልግበትና ይኸንንም የጤና ክትትል ከእቅዱ መካፈያ ሰአታት ውጭ ለመድረግ አመቺ በማይሆንበት ወቀት ለማስተዋወቂያው ተካፋይነት ከሚከፈለው ክፍያ ጋር ፈቃድን የማግኘት መበት አሎት ። በእርግዝና ወቅት እስከ አስር ቀናት ድረስ የማስተዋወቂያ እቅዱ ተካፋይነት ክፍያውን እያገኙ ፈቃድ የማግኘት መብት አልዎት ።

*ጡት ለማጥባት ፍቃድ*

ልጅዎን የሚጠቡ ከሆነ በልጁ የመጀመሪያ ዓመት እድሜ ውስጥ በየቀኑ ጡት በማጥባት እስከ አንድ ሰዓት ድረስ የማስተዋወቂያውን እቅድ ተዳፋይነት ክፍያ አያገኙ የማጥቢያ ፈቃድ የማግኘት መብት አሎት ።

### በወሊድ እና በጉዲፈቻ ልጅ ሲኖርዎት የማስተዋወቂያ እቅዱ ክፍያ ሳያገኙ ፈቃድ

ልጅ ከወለዱ በኋላ በማስተዋወቂያ እቅዱ  መርሃግብር ውስጥ የሚሳተፉ ወላጆች በልጁ የመጀመሪያ ዓመት እድሜ ውስጥ በአጠቃላይ እስከ አሥር ወር ድረስ ልጁን ማሳደጊያ የእረፍት ፈቃድ የማግኘት መብት አላቸው ፡፡ አንዲት ሴት ከወለደች በኋላ ወይም ጉዲፈቻ በኋላ በእረፍት ፈቃድ ላይ እያሉ አውራጃው የክትትል እና የኖዊጂያን ቋንቋ ሥልጠና ወይም የቋንቋ ልምምድ እድል ያቀርባል ፡፡ ከአውራጃው የሚቀርበው እድል የሚቀርበው ከእረፍት ከተወሰደበት ከአራተኛ ወር ጀምሮ ሲሆን እንደዚሁም  ለእርስዎ ተስማሚ በሚሆንበት መንገዱ መሆን አለበት።

ጉዲፈቻን በተመለከተ የመተዋወቂያ እቅዱን ተሳተፉ አሳዳጊ ወላጆች ልጁ ከ 15 ዓመት በታች ከሆነ በአጠቃላይ እስከ አስር ወር ድረስ የእረፍት ፈቃድ የማግኘት መብት አላቸው ፡፡ ሁለቱም ወላጆች የማስተዋወቂያ እቅዱ መርሃግብር ውስጥ ተሳተፊ በሚሆኑበት ጊዜ 75  የእረፍት ቀናት ለአባት እና ለ 75 ቀናት ደግሞ ለእናት የማግኘት መብት አላቸው ፡፡ አባትየው የእረፍት ቀናቱን የማይጠቀም ከሆነ ግን ያልፋል ማለት ነው ፡፡ ነገር ግን አባትየው በህመም ወይም በጉዳት ምክንያት ልጁን ለመንከባከብ ሙሉ በሙሉ የማይችል ከሆነና እርዳታ የግደ ማግኘቱ አስፈአላጊ ከሆን  ይህ ድንጋጌ አይጸናም ። ይህ ግ ን በሀኪም መግለጫ መረጋገጥ ይኖረበታል ፡፡

#### የእረፈት መጠየቂያ ማመልከቻ

ለምሳሌ ወደ ሐኪም ቤት ወይም የጥርስ ሐኪም፣ ለስራ የቃል መጠይቅ ለመስጠት ወይም ለሌላ ነገር አጠር ላላ ጊዜ ከተሳታፊትነት ለመቅረት ከአውራጃው መንግስታዎ የፈቃድ (Velferdspermisjon)እንዲሰጥዎ ማመልከት ይችላሉ ።

እንደዚሁም ልጆች ለመጀመሪያ ግዜ ትምህርት ቤት ወይም አጸደ ህጻናት መዋያ ሲጀምሩ ወይንም በቤተሰብ ውስጥ ሓዘን በሚኖርበት ወቅት መንግስታዊ ፈቃድን እንዲሰጥ ማመልካተ በጨማሪም ይቻላል ። ተጨማሪና ጠለቅ ያለ  ምግለጫ ይህን መሚመለከት ከፈለጉ ከመርሐ ግብሩ አማካሪዎ ሊያገኙ ይችላሉ።

ከሐኪም በሚሰጠው የጤና መራጃ ላይ በመመስረት እርሶ ወይም ልጆዎ ለረዘም ላላ ጊዜ በሚታመሙበት ወቅት የማስተዋወቂያውን መርሐ ግበርን ከመካፈል ነጻ ለመሆን ፈቃድ ለመጠየቅ የማመልከተ መብት አሎት። እስከ አንድ አመት ድረስ ምንም አይነት የተካፋይነትን አስተዋጽዎን ሳይከፈሉ ፈቃድን ማግኘት ይችላሉ።

## የእረፍት ቀናትና በአላት

ቅዳሜና እሁድ ሁሉም ተካፋዮች ከመስተዋወቂያው መርሐ ግብር ተሳታፊነት ነጻ ናቸው።

ከዚህ በታች የሚከተሉት ቀናት የኖርዌ መንግስታዊ የበአላት ቃናት ናቸው። ስለዚሕም ተካፋዮቹ ከተካፋይነት ነጻ ናቸው።

ሚያዚያ 23 ግንቦት 9 (17. ና 1.ማይ) ፣ 1ኛ የአዲስ አመት ቀን፣ ጸሎተ ሀሙስ፣ ስቅለት ፣2ኛ የፋሲካ ቀን፣ እርገት ፣2ኛው ፐራቅሊጦስ እና 1ኛ እና 2ኛው የገና ቀን።

የኖርዊጅያን ቤተክርስቲያን አባል ከአልሆኑ ግን በአንድ አመት ውስጥ እስከ ሁለት ቀናት ድረስ ከማስተዋወቂያ መርሐ ግብር ከተካፋይነት ከአስተጽዎ ጋር በሐይማኖታዊ በአላት ለማክበር ወይም ለመካፈል ከተካፋይነታቸው ነጻ መሆን ይችላሉ ሖኖም ግን ይህ የበአልዎ ቀን ከመድረሱ 14 የስራ ቀናት በፊት ቀደም ብሎ ለአውራጃው ማስታወቅ ያስፈልጋል።

## እረፈት

በየአመቱ የ25 ቀናት እረፍት የማግኘት መብት አሎት። ይህ የእረፍት ወቅት መቼ እንደሚሆን የሚወስነው አውረጃው ይሆናል። በረፍቱ ወቅት የማስተዋወቂያ ተሳታፊዎች አስተዋጽዎ የማግኘት መብት አሎአቸው።